| | | |
|---|---|---|
| **የአሌክሳንደሪያ ከተማ፣ የቨርጂኒያ ሳኒቴሽን ባለስልጣን ቦርድ የፀደቀ ፖሊሲ** | | AlexRenew |
| ርዕስ: የአካባቢ ፍትሕ | | |
| የፀደቀበት ቀን: ታሕሳስ 19, 2023 | የተሻሻለበት ቀን: | ገጽ 1 ከ 1 |

AlexRenew ስራዎቹ በሚያገለግለው ማህበረሰብ ላይ የሚያደርሱትን ያልተመጣጠኑ የአካባቢ ተጽእኖዎች ለመከላከል እና ለማቅለል የአካባቢ ፍትሕ ግቦቹን እንደሚከተል ያረጋግጣል እንዲሁም ይተጋል። AlexRenew ሁሉም ሰው በተመጣጣኝ ዋጋ ደህንነቱ የተጠበቀ የንፅህና አጠባበቅ እና ንፁህ የውሃ መስመሮችን የማግኘት መብት እንዳለው፣ ማንኛውም ቡድን ያልተመጣጠኑ የአካባቢ ጫናዎችን መሸከም እንደሌለበት እና ሁሉም ቡድኖች በAlexRenew ፕሮግራሞች ከሚመጡ የአካባቢ ማሻሻያዎች ፍትሃዊ ተጠቃሚ መሆን እንዳለባቸው በጥብቅ ያምናል።

የአካባቢ ፍትህ በምናገለግለው ማህበረሰብ ላይ ያልተመጣጠኑ የአካባቢ ጫናዎችን ሳንፈጥር የማህበረሰቡን የቆሻሻ ውሀ በማስተዳደር ረገድ ተልእኳንን ወደፊት ማራመድ ያስችለን ዘንድ ሁሉንም ዘሮች፣ ባህሎች፣ የአኗኗር ዘይቤዎች፣ መኖሪያ መንደሮችና ገቢዎችን ጨምሮ የነዋሪዎቻችን ፍትሀዊ አያያዝ እና ትርጉም ያለው ተሳትፎ ነው። የአካባቢ ፍትህ ስራችን የታሰበበት እና ውጤት የሚያመጣ መሆን አለበት።

AlexRenew የማህበረሰቡን የቆሻሻ ውሀ ለማስተዳደር የተቋቋመ ባለ አንድ ዓላማ አገልግሎት ሰጪ እንደመሆኑ የማህበረሰብ ጤናን ለመጠበቅ እና አካባቢን ለማሻሻል የተዘጋጁ መሰረተ ልማቶችን ተጠቅሞ ይሰራል እንዲሁም ይጠብቃል። የAlexRenew የአካባቢ ፍትህ ቁርጠኝነት ማህበረሰባችንን በተሻለ ሁኔታ ለማገልገል ትርጉም ባለው ተሳትፎና በመረጃ በተደገፉ እርምጃዎች ይመራል። በመሆኑም AlexRenew የአካባቢ ፍትህ ግቦችን ለማሳካት ለሚከተሉት እርምጃዎች ይተጋል፡

- በምናገለግለው ማህበረሰብ ላይ ሊኖሩ የሚችሉ ማንኛውንም ያልተመጣጠኑ የአካባቢ ልዩነቶች ለመለየት የAlexRenewን አሁን ያሉ መሰረተ ልማቶች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ይገመግማል። የትግበራ የጊዜ ሰሌዳዎችን ጨምሮ በስራዎችና የካፒታል ኢንቨስትመንቶች አማካኝነት እነዚህን ልዩነቶችና ተጽኖዎች የሚቀርፉ ስትራቴጂዎችን ያዘጋጃል።
- ሰራተኞች ስለ AlexRenew ፕሮግራሞች አስፈላጊነት፣ ጉዳዮች እና ተጽኖዎች/ ውጤቶች ለመረዳት የሚያስፈልጓቸውን አስፈላጊ ምንጮች መታጠቃቸውን ለማረጋገጥ በመደበኛነት የአካባቢ ፍትህ ስልጠና ይሰጣል።
- የአካባቢ ፍትህ ታሳቢዎች፣ ስነ ሥርዓቶችና ውጤቶችን በተገቢ የAlexRenew ፕሮግራሞች ውስጥ ለማካተት የሚያስችል መመሪያ አዘጋጅቶ ይተገብራል።
- በማህበረሰቡ ላይ ተጽእኖ በሚፈጥሩ በሁሉም የፕሮግራሞቹ ዋና ዋና ዙሮች ወቅት የማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ተጋላጭ ነዋሪዎችን እና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ በዝቅተኛ ደረጃ የተወከሉ ቡድኖችን ጨምሮ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ባለድርሻ አካላትን ትርጉም ባለው መልኩ ያሳትፋል።
- ከAlexRenew ፕሮግራም ጋር ተያያዥ የሆኑ የማህበረሰብ ተጽእኖዎችን ለመረዳት በንቃት ያዳምጣል።
- ባለድርሻ አካላት በማህበረሰባችን ላይ ተጽእኖ በሚፈጥሩ ውሳኔዎችና እርምጃዎች ላይ መሳተፍ መቻላቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ እና ለባህል አግባብነት ያላቸው የግንኙነት ስትራቴጂዎችን ያዘጋጃል።
- ነዋሪዎችን በንጹህ ውሀ ላይ ስለሚያደርጉት ኢንቨስትመንት ጠቀሜታ እንዲረዱ ለማስቻል አሳታፊና ታስቦባቸው የሚዘጋጁ የትምህርት ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል።
- ውሳኔዎችን የማህበረሰቡን ነዋሪዎች፣ ታሪክ እና ኢኮኖሚ በመገንዘብ ያሳልፋል።
- ከከተማውና ሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ጋር በመሆን ለሚያስፈልጋቸው አካላት የፋይናንስ ድጎማ የሚያደርጉ ኢኒሺየቲቮችን ከመተግበርና ከማሳካት ጎን ለጎን ፍትሀዊና ዋጋቸው ተመጣጣኝ የፍሳሽ ተመኖችን የሚደግፉ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ስትራቴጂዎችን ያዘጋጃል።
- እንደ ዋና ዋና ፕሮግራሞቹ አንድ ክፍል ተገቢና ተግባራዊ ከሆነ የተጎጂ ማህበረሰቦችን ታሪክ ለመንገር እንዲረዳው የማህበረሰብ ጥቅማ ጥቅም ለማቅረብ ከአሌክሳንደሪያ ከተማ ጋር በትብብር ይሰራል።
- ለአሌክሳንደሪያ ከተማ እና ሌሎች የመንግስትና የግል ተቋማት የዋጋ ተመጣጣኝነትና የአካባቢ ፍትህ ኢኒሺየቲቮችን ለማዘጋጀትና ለመደገፍ እንዲችሉ ከማህበረሰብ ተኮር፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ፣ እምነት ተኮር ድርጅቶች እና የንግድ ድርጅቶች ጋር ዋና ዋና ግንኙነቶችን እንዲመሰርቱ፣ እንዲያጠናክሩ እና ይህን ይዘው እንዲቀጥሉ ድጋፍ ያደርጋል።
- አዲስ እውቀት ሲገኝ ተመራጩን ያለውን መረጃ በመጠቀም የAlexRenew ፕሮግራሞችን ቀጣይነት ባለው መልኩ ያሻሽላል።